# Learning by Ear 2013

**"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ"-"መዘዙን መቀበል"**

EPISODE 24: **ያልተጠበቀው መጨረሻ**

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: አቶ ሙላቱ RELEASED**

- **መርማሪECTOR ርብቃ (F, 40s)**
- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **COP (M, 35)**

**SCENE 2: THE አቶ ጃለታና ባለቤቱ MEET አቶ ሙላቱ**

- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **MRS. ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)**
- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**

**SCENE 3: ምህረት COMPLAINS ABOUT EATING MEAT**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ብሩክ (M, 8)**
- **ወ/ሮሉሊት (F, 40)**

**SCENE 4: አቶ ጃለታ CALLS አቶ መኩሪያ**

- **አቶ ጃለታ (M, 45)**

- *አቶ መኩሪያ* **(M, 45)**

## INTRO

## 1. NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ስለ አፍሪቃውያን ታዳጊ ወጣቶች የሚተርከዉና ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ተከታታይ ትምህርታዊ ድራማ ነዉ። ዛሬ "መዘዙን መቀበል" በተሰኘዉ ሁለተኛ ዙር ድራማ ሃያ አራተኛው ክፍል ላይ ደርሰናል። የምህረት እናት፣ ወ/ሮ ሉሊት ከአካባቢው የወጣት ማዕከል ወጣት ሴቶች ድንገት ቤታቸው መከሰታቸው አስደንቋቸው ነበር። የወጣት ማዕከሉን ቡድን እየመራች ያመጣችው ከላቦሪያ በትምህርት ልውውጥ መረሃ-ግብር ቦንን አካዳሚ የገባችው የአቻ ለአቻ አማካሪዋ አልማዝ ነበረች። ቡድኑ ለወ/ሮ ሉሊትም ጥሩ ምክር ሰጥቶዋል…

## 2. EPISODE 23, LINES 94 – 108:

<u>አልማዝ</u>*:* ግን እኮ የምህረት እናት ትንሽ ስራ ነገር ቢኖርዎ እስኪ አስቢው… …

<u>ወ/ሮሉሊት</u>: አሀ፣ በርግጥ ጥሩ ነበር። ግን አይቻልም።

<u>አልማዝ</u> ***(108):*** ከገጠር አካባቢ አታክልቶች ብታመጪ እና እዚህ ከተማ ውስጥ ብትሸጪስ?

## 3. NARRATOR:

**እለእዚህ ጉዳይ ከተወያዩ ትንሽ ጊዜ አልፏል፡፡ እስኪ የወ/ሮ ሉሊት እቅድ ሰርቶ እንደሆነ እንመልከት! የምህረት አባት አቶ ሙላቱስ እንዴት ይሆኑ? ባለፈዉ ስለ እሳቸው የሰማነዉ በፖሊስ ጣቢያ ታስረው እንደ ነበር ነዉ፡፡ አቶ ሙላቱ የምህረት የክፍል ጓደኛ የሆነውን የንጉሤን ቤተሰቦች፣ ዘርፈዋል በሚል ተከሰው ታስረዋል! ሆኖም አቶ ሙላቱ ከደሙ ንፁህ ናቸው። ይልቁንስ ከዚህ ሁሉ ሴራ ጀርባ የአካባቢው ባለስልጣን የአቶ መኩሪያ እጅ ነው ያለበት፥**

***KW BEGIN***

## 4. EPISODE 7, LINES 105 - 108:

<u>**አቶ መኩሪያ:**</u> **ኦፊሰር ገንዘቡ የውልህ፡፡ አሁን አቶ ሙላቱ ላይ ለዘለአለም እኔ ዘረፋውን እንዳጠነጠንኩበት ማንም ስለማያውቅ እስከመጨረሻዉ አስገብተህ ከርችምና እንዲበሰብስ አድርግልኝ፥**

<u>**ሙሉጌታ:**</u> **አቶ ሙላቱ ለረጅም ጊዜ ከዚህ እንደማይወጣ አረጋግጥልዎታለሁ!**

***KW END***

## 5. NARRATOR:

**ዛሬ የሚቀርበዉ ድራማ “ያልተጠበቀው መጨረሻ” የተሰኘ ርዕስ ይዟል። ታሪኩ የሚንደረደረውም አቶ ሙላቱ በስተመጨረሻ ከእስር ቤት ሲለቀቁ ነው…**

## <u>SCENE 1: አቶ ሙላቱ RELEASED</u>

## 6. SFX: POLICE STATION ATMO

## 7. SFX: RUMMAGING IN BAG

**8.** መርማሪ ርብቃ: አቶ ሙላቱ እዛ ቦርሳ ውስጥ ንብረትዎ በአጠቃላይ መኖሩንአረጋግጠዋል?

**9.** አቶ ሙላቱ: መርማሪ ርብቃ፣ ሰዓቴን አላገኘሁትም

**10.** መርማሪ ርብቃ: **(calls)** ኢንስፔክተር!

**11. COP:** **(from a distance)** አቤት መርማሪ?

**12. SFX: FOOTSTEPS - COP APPROACHING**

***KW BEGIN***

**13.** መርማሪ ርብቃ: እስረኞች በእስር ቤቱ ሲቆዩ የእስረኞችን ንብረት በተመለከተ ሀላፊውማን ነው?

**14. COP:** **(on mic)** አብዛኛውን ጊዜ በቁጥጥር ስር ያዋለው ፖሊስ ነው፡ .

***KW END***

**15.** መርማሪ ርብቃ: የእዚህ ሰውዬ ሰዓት ጠፍቷል የምታውቀው ነገር አለ?

**16. COP:** አላውቅም እመቤቴ፡፡ የእዚህ ጉዳይ ተጠሪ መርማሪ ፖሊስ ሙሉጌታ ነበር፡ .

**17.** መርማሪ. ርብቃ: **(not amused)** ጭራሽ ይህንንም? እንዴ! አቶ ሙላቱን በሀሰት ክስ ዘብጥያ መወርወሩ አይበቃውም ነበር? እነዚያ ሁለት ወሮበሎች እራሳቸው መጥተው እጃቸውን ባይሰጡ ኖሮ እኮ ይሄኔ የቀድሞው መርማሪ ፖሊስ ሙሉጌታ ከእዛ የምክር ቤት ተብዬ መኩሪያ ጋር

የሸረቡትን ሴራ ማንም ማንም መፍታት አይችልምም ነበር! ስለ ሙስናው ብዙ ነገር ሰምቻለሁ! መርማሪ አባክህን ሙሉጌታን ፈልገህ አምጣልኝ! ለእኚህ ሰው ሰዓታቸውን ሊመልስላቸው ይገባል፡፣

**18. COP:** ግን እመቤቴመርማሪ ሙሉጌታ አንቺ ሳታባርሪው ፖሊስ ጣቢያውን ለቅቆ ወጥቷል። የት እንዳለ እንኳ አናውቅም፣

**19. መርማሪ ርብቃ:** ፖሊስ ነህ፣ አይደለህም? ስራህ ወንጀለኞችን አሳድዶ መያዝ ነው! የቀድሞ መርማሪ ሙሉጌታ የሙስና ክሶችን መጋፈጥ ይጠበቅበታል። ስለዚህ አሁኑኑ ፈልገው!

**20. COP:** እሺ እመቤቴ .

**21. SFX: FOOTSTEPS AS COP LEAVES**

***KW BEGIN***

**22. መርማሪ ርብቃ:** (to አቶ ሙላቱ) የፖሊስ መኮንን ዜጎችን ማገልገል እና መጠበቅ ነው እንጂ ሊያበሻቅጣቸው እና ሊሰርቃቸው አይገባም። አቶ አቶ ሙላቱ በቁጥጥር ስር ያዋሎት ፖሊስ በሚገባ እንደሚያውቀው ያለ ጥፋትዎ በዘረፋ ወንጀል ተከሰው እዚህ እስር ቤት በመቆየትዎ በፖሊስ መምሪያው አጠቃላይ አባላት ስም ይቅርታ ልጠይቅህዎ ብቻ ነው የምችለው። (sighs) እባክዎን እዚህ ላይ ይፈርሙልኝ

**23. SFX: PEN WRITING ON PAPER**

**24. አቶ ሙላቱ:** ይኸው እመቤቴ ፣

**25. SFX: PAPER HANDED OVER**

***KW END***

**26.** መርማሪ ርብቃ: አቶ አቶ ሙላቱ አሁን ነጻ ነዎት፤ መሄድ ይችላሉ።

**27.** አቶ ሙላቱ: አመሰግናለሁ መርማሪ ርብቃ፤

**28.** መርማሪ ርብቃ: **(continues)** አቶ ሙላቱ፤ ግን ቅድመ-ሁኔታዎች እንዳሉ ያስታውሱ።

የራስዎትን ልጅ ለአቶ አቶ መኩሪያ መሸጥዎን አምነው ቃል ስለሰጡ ለዚያ መቀጣት ይኖርብዎታል። ከአሁን ጀምሮ በየእለቱ ፖሊስ ጣቢያ ብቅ እያሉ መኖርዎን ያሳውቃሉ፣ ፍርድ ቤት መቼ እንደሚቀርቡ እናሳውቅዎታለን።

**29.** አቶ ሙላቱ: እሺ መርማሪ ርብቃ፤

**30.** መርማሪ ርብቃ: እና ባለቤትዎየሚገኙበትን ቤት ከ30 ሜትር ርቀት መቅረብ አይችሉም። እሷም ልታይዎ እንደማትፈልግ እንድንነግርዎ ጠይቃናለች፤ ፡ በወር አንድ ጊዜ ልጆችዎን ማየት የተፈቀደልዎ ቢሆንም ከእሷ ጋር ወይም ከእነሱ ጋር እንዲኖሩ ግንአልተፈቀደልዎም። ገባዎት?

**31.** አቶ ሙላቱ: **(sighs)** አዎ እመቤቴ፤ .

**32.** መርማሪ ርብቃ: እሺ፤ መሄድ ይችላሉ።

**33. SFX: FOOTSTEPS** አቶ ሙላቱ **LEAVE**

**34. MUSICAL INTERLUDE (OR FADING OF ATMOS)**

**SCENE 2: የአቶ ጃለታ ቤተሰብ MEET አቶ ሙላቱ**

**35. ATMO: OUTSIDE THE POLICE STATION (PEOPLE TALKING, POLICE RESPONDING TO EMERGENCIES ON WALKIE-TALKIES, SIRENS HEARD)**

**36.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ጃለታ፣ ውድ ባለቤቴ፣ ዛሬ በእውነት አቶ ሙላቱን ለቀውታል?

**37.** አቶ ጃለታ : የሰማሁት እንደሱ ነው…

**38. MRS.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ምስኪኑን ሰው እስር ቤት በመወርወራችን ጥፋተኝነት ተሰምቶኛል፡፡ ይህን ሁሉ ጊዜ በቤታችን ለተፈጸመው ዘረፋ ተጠያቂው እሱ እንደሆነ እራሳችንን አሳምነን ነበር!!

***KW BEGIN***

**39.** አቶ ጃለታ : እስር ቤት አልነበረም፡፡ ፖሊስ ጣቢያ ተይዞ ቆይቷል፡

**40.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : አንተ ደሞ፤ ያው ማለት እንደሆነ ጠንቅቀህ ታውቃለህ፡

***KW END***

**41.** አቶ ጃለታ : ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው የወንድ ጓደኛሽ ነው፡

**42.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : **(not amused)** ምን ማለትህ ነው የወንድ ጓደኛሽ ስትል? ይህንን ሁሉ ዘመን አግብተኸኝ ስትኖር በአንድ ወቅት ከአቶ መኩሪያ ጋር የነበረኝን ግንኙነት ልትረሳው አልቻልክም?

**43.** አቶ ጃለታ : ይህንን ዘረፋ አንቺን እንድመልስለት እንዳቀናበረው እርግጠኛ ነኝ። ያ ካልሆነ ለምን ያደርገዋል?

**44.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ስሜት አይሰጥም! እንደዉም አልገባኝም። ግን ይሄ የተከሰተው ድሮ ገና በአንድ ወቅት ለተደረገ ነገር ነው ብለህ በእውነት ታስባለህ?

***KW BEGIN***

**45.** አቶ ጃለታ : ሌላ ምንም ላስብ አልችልም… **(convinced)** አልችልም። ወደ እኔ ሊመለስ ፈልጓል! እርግጠኛ ነኝ! እሱ ያፈቀርሽ እንደነበር እያወቀኩ እንዳገባሽ በመጠየቁ አሁንም ድረስ ይወቅሰናል። **(sighs)** እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በፖለቲካ ስራ ብዛት እና ትንሽዬ ሴት ልጁ የተደሰተ መስሏል…

***KW END***

**46. MRS.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : **(sees** አቶ ሙላቱ**)** እንዴ፣ ተመልከት፣ አቶ ሙላቱ ያውልህ! ጉድ አምላኬ! በጣም ከስቷል። **(shouts)** ሠላም፤፤አቶ ሙላቱ እዚህ ነን!

## 47. SFX: FOOTSTEPS APPROACH ON PAVEMENT

**48.** አቶ ሙላቱ: **(approaching, sarcastic)** ነው! ድንቅ! አቶ ጃለታ እና ወ/ሮ ዘዉዲቱ ግን ከእኔ ምንድን ነዉ የምትፈልጉት? ወደ እስር ቤቱ መልሳችሁ ልትልኩኝ ነው?

**49.** አቶ ጃለታ : አቶ ሙላቱ ስለተከሰተው ነገር በእውነት ይቅርታ ልንጠይቅህ እንፈልጋለን። ፖሊስ እራሳቸው ሄደው ቃላቸውን ስለሰጡት ዘራፊዎች ነግሮናል። አሁን ከዘረፋው እና ከድርጊቱ ጀርባ አቶ መኩሪያ እንዳለበት እና አንተ ንጹህ እንደሆንክ አረጋግጠናል፡ .

**50. MRS.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : እንደተጸጸትን ለማሳየት ምንም ነገር ብትፈልግ የፈለከውን ነገር እናደርግለሀለን!

**51.** አቶ ሙላቱ: **(sighs)** ማረፊያ ቦታ እፈልጋለሁ።

**52. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 3: ምህረት COMPLAINS ABOUT EATING MEAT

**53. ATMO: TANDIKA SLUMS, DAYTIME**

**54. SFX: IRON PLATES AS THEY EAT**

***KW BEGIN***

**55.** ወ/ሮሉሊት: **(full mouth)** ብሩክ፣ ብላ! ሀኪሙ መጠንከር አለብህ ብሏል። ገና ከሳንባ በሽታ ሙሉ ለሙሉ አልተሻለክም፤ እያገገምክ ነው ገባህ!

**56.** ብሩክ: **(full mouth)** እሺ እማ

**57.** ወ/ሮሉሊት: አንቺም ምህረት፣ ነፍሰጡር እናት ምግብ ያስፈልጋታል፡ .

***KW END***

**58.** ምህረት: እማዬ ያንን የአትክልት መሸጫ ከከፈትሽ ጀምሮ የምንበላው ስጋ ብቻ ነው፡

**59.** ወ/ሮሉሊት: ምንም ገንዘብ ስላልነበረን ጎመን እና ጣዕም አልባ አጥሚት ስንቀለብ መኖራችንን ረሳሽው? አሁን ብዙ ስጋ በመብላትሽ ቅር ይልሻል?

**60.** ምህረት: ለለውጥ ያህል አሳ ልትገዢ ትችያለሽ። ሰውነትን ለመገንባት በጣም ጠቃሚ የሆነ የምግብ ይዘት አለው!

**61.** ወ/ሮሉሊት: **(laughs)** ውይ! ምህረት፣ አንቺ እና መጽሀፎችሽ! ደግሞ ልክ እንደሆንሽ እርግጠኛ ነኝ። እኔ ግን ስጋ የተሻለ ይመስለኛል። በእዛ ላይ ወንድሞችሽ ስጋ ይወድዳሉ። ብሩክን ተመልከቺው!

**62.** ብሩክ: **(full mouth)** ልክ ነው። በጣም እወዳለሁ!

**63.** ወ/ሮሉሊት: **(laughs)** እናም ቅዱስ ትንሹ ነጋዴያችን፣ ልክ እንደገባ ይዞ ይሰለቅጠዋል።

**64.** ምህረት: በነገራችን ላይ ቅዱስ የት አለ? ከሙሴ ጋር እንደገና ወደ ገጠር ሄደ እንዴ?

**65.** ወ/ሮሉሊት: አዎ። ከቤተሰቤ እርሻ የሚያመጡልኝን አትክልቶች መቆጣጠሩ በጣም ያስደስተዋል።

**66.** ምህረት: ደስ ይላል። ግን ታውቂያለሽ፣ እማዬ፣ ቅዱስ እና ብሩክ ትምህርት ቤት መግባት አለባቸው፡

**67.** ወ/ሮሉሊት: ሁሉም ሰው እንደ አንቺ ነጻ የትምህርት እድል አያገኝም። ገንዘብ እያጠራቀሙኩ ነዉ፤ ምናልባት በሚቀጥለው አመት ይጀምራሉ፤

**68.** ምህረት: ዛሬ አባዬን ከፖሊስ ጣቢያ ይለቅቁታል። ምን አልባት ስራ ያገኝ እና የሁለታችሁም ገቢ ተቀናጅቶ የትምህርት ቤት ወጪያቸውን ይሸፍናል፤ .

**69.** ወ/ሮሉሊት: **(not amused)** ስለ ሙላቱ ምንም ነገር አትንገሪኝ!

**70.** ምህረት: ግን እኮ አባታችን ነው፤

**71.** ወ/ሮሉሊት: ምህረት፣ አባታችሁ ተመልሶ እዚህ ቤት አይገባትም፤

***KW BEGIN***

**72.** ምህረት: ግን፣ እማዬ…

**73.** ወ/ሮሉሊት: **(commanding)** ያን እርሺው፣ ምህረት ስለዚህ ጉዳይ ቀደም ሲል ተነጋግረናል**(proudly)** በፊት ባይመስለኝም አሁን ብቻዬን ቤተሰቤን መንከባከብ እችላለሁ፤

**74.** ምህረት: **(sulks)**

***KW END***

**75. MUSICAL INTERLUDE**

__**SCENE 4:** አቶ ጃለታ **CALLS** አቶ መኩሪያ__

**76. ATMO: AT THE JUMBES', INTERIOR, EVENING**

**77. SFX: CELL PHONE DIALLING, CALLING TONE**

**78.** አቶ መኩሪያ: **(answers at the other end, on phone)** ሄሎ? መኩሪያ ነኝ፡

**79.** አቶ ጃለታ : ሄሎ፤ጃለታ ነኝ።

**80.** አቶ መኩሪያ: **(short pause)** እሺ፣ ጃለታ፣ ምን ተገኘ ባክህ? ስንት ዘመናችን በል ጃል!

**81.** አቶ ጃለታ : **(not amused)** በል አሁን ይሄ ዝባዝንኪህን አቁም መኩሪያ፣ ። ዛሬ ማንን እንዳገኘሁ ገምት እስኪ? አቶ ሙላቱን፤ ሁሉንም ነገር ሰምቻለሁ፡

**82.** አቶ መኩሪያ: ምንድን ነው የምትቀባጥረው፣ ጃለታ? በቀጥታ መናገር አትችልም? ጊዜ የለኝም። አንዳንዶቻችን ገና ስንት ስራ አለን፡

**83.** አቶ ጃለታ : የምታደራጃቸውን ሌሎች ዘረፋዎች ማለትህ ነው? እንደ አቶ ሙላቱ አይነቱን ምስኪን ዘበኛ ወኽኒ ቤት ለመወርወር?

**84.** አቶ መኩሪያ: **(silent)**

**85.** አቶ ጃለታ : ዘውዲቱን ካገባኋት ከዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላም ቂም እንደቋጠርክ ነህ?

**86.** አቶ መኩሪያ: **(laughs)** በእዚህ ያረጀ ያፈጀ ታሪክ እጄን የማቆሸሸ ይመስልሀል? **(pause)** ካነሳኸው አልቀረ ግን የሴት ጓደኛዬ እንደነበረች ታውቃለህ፤ እናስ ያ እሷን ከማግባት ገታህ? አልገታህም፡፡ **(deep breath)** ከዚያ በፊት የልብ ጓደኛዬ ነበርክ፣ ጃለታ፣

***KW BEGIN***

**87.** አቶ ጃለታ : ዘውዲቱ ያኔ ስለ ራሷ መወሰን የምትችል ኮረዳ ነበረች። ውሳኔው የራሷ ነበር፡፡ እናም እኔ ለአንተ ያለኝ ምክር ደግሞ አንተ ያንን ውሳኔዋን አክብረህላትእንድትቀጥል ነው መኩሪያ! ሰማኸኝ?

**88.** አቶ መኩሪያ: አልሰማህም! ገና አላበቃም ጃለታ፣

***KW END***

**89.** አቶ ጃለታ : መኩሪያ፣ አሁን እየተነጋገርን ባለንበት ቅፅበት ፖሊሶች ሊወስዱህ እየመጡ ናቸው፣

**90.** አቶ መኩሪያ: **(laughs)** ስለእዚያ በጣም እርግጠኛ መሆን አልችልም፣| .

**91.** አቶ ጃለታ : ውይ ...ስለ ጓደኛህ ፖሊስ ሙሉጌታ መባረርስ ጠቅሼልሀለሁ?

**92.** አቶ መኩሪያ: **(shocked)** ምን? **(pulls himself together)** ኹህ-፣ለነገሩ ጓደኛዬ እሱ ብቻ አይደለም፡፡ ምን ማለቴ እንደሆነ ከገባህ...

**93.** አቶ ጃለታ : መልካም ህይወት፣ አቶ መኩሪያ፡፡ እስር ቤቱ እንደሚመችህ ተስፋ አደርጋለሁ፣

**94.** አቶ መኩሪያ: ዜድን ሰላም በልልኝ!

## 95. SFX: PHONE REPLACED

## 96. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>

**ምን አይነት የተገለባበጠ ክስተትነው! አቶ መኩሪያ እና ጃለታ አንድ ትምህርት ቤት የተማሩ ጓደኛማቾች ይመስላሉ! በአንዲት ሴት ተጣልተው ነበር- ልክ የጃለታ ልጅ ንጉሴ ከክፍል ጓደኛው ዳንኤል ጋር በምህረት እንደተጣሉት…ታሪኩ ወዴት እንደሚያመራ እና በነምህረት ቤተሰብ ላይ ምን እንደሚከሰት ለማወቅ ከፈለጉ የድራማውን ቀጣይ ክፍል ጠብቀው ይከታተሉ። የዛሬዉን ድራማ የድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ በድጋሚ ማድመጥ ይቻላልል። ድራማዉን በግል መዝገቦ ላይ ለመገልበጥም ድረገፃችንን ይጠቀሙ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። ጤና ይስጥልን!**